# ታማኝ ውሻ

ላበላህ ጌታ የምታድር
አፍህ ከያዘ አይጠረጥር
ታማኝ ችሎማደር፤
ሻጭና ገዥ ሲስማሙብህ
ከፍ ቢደረግ ዋጋህ
ወይም ዝቅ ቢልብህ
ማንም ሸጦ ቢሰድህ
ወይም ገዝቶ ቢወስድህ
ካልጎደለብህ ሆድህ
ችሎ ማደር ምን ገዶህ?።
ደግሞ አዲሱ ጌታህ
አንገትህን ቢያሥርህ
ወዳሸበት ቢጎትትህ
በጭለማ ቢያኖርህ
መታዘዝ እንጂ እምቢ የለህ።
ለማይፈልጓቸው
እንድትጮህባቸው
ለሚፈልጓቸው
እንዳትታያቸው
ተዘግተህባቸው
እንዳትለይ አይተህ
ተከልሎ አይንህ
እንደፍላጎትህ
መራመድ ተነሥቶህ
እናት ቢጣልብህ
አባት ቢጠፋብህ
ልጆች ቢሸጡብህ
ቢበታተኑብህ
ለአውሬ ቢሰጡብህ
መሸጥ መለወጥህ
ሆኖ መች ቀረልህ?
ማሰብና አቅልህ
ጨርሶ ተነፍጎህ
ጌታህ አሰማርቶህ
እንድትይዝ ሲያዝህ
ደግሞ ንከስ ሲልህ
መች ትመለሳለህ?
ሁልጊዜ እያሳደድኽ
የዱር ሀብት እያደንኽ
የሰው ከብት አልቀረህ
ለምታምነው ጌታህ
ግዳይ እየጣልህ
ሐፍረት ሳይኖርብህ
ታፈረ እየተባልኽ
እንዴት ትኖራለህ?
ሰዎች እየበደልኽ?
የራስ ውሻ መቼም ጌታውን ያውቃል
ቢያሥሩት ቢያንገላቱት የግድ ይታዘዛል
እንደ የሰው ውሻ ከቶ ምን ይከፋል?
ቹ! ቹ! ከተባለ ለማን ይመለሳል?
ወንድምህን ሲያሥሩት
ገርፈው ሲያንገላቱት
ጎጆህን ሲያፈርሱት
ዘርህንም ሲያጠፉት
አልተሰማህ ፀፀት
አይሰማህ ውርደት
ይሉኝታና ሐፍረት
አያውቅህም ቅሌት
ለሆድህ መገዛት
ለምትኖረው ሕይወት
ጌታህ እንዲደሰት
ጭራህን በመቁላት።
ታሥረህ በሰንሰለት
በተዘጋብህ ቤት
ያለችህ ነፃነት
በልቶ ማንቀላፋት።
ያለህ ትልቅ ብልኃት
ሥጋን ቀብሮ መብላት፤ ሥጋን ቀብሮ መብላት።
ለጌታህ ደህንነት
ቢሰበር ያንተ አጥንት
ቢፈርስ ያንተ አንጀት
ብትረባ ብትሞት
ማነው የሚያስባት
ያንተን ጤና ሕይወት
ይናንተን ነፃነት?
አወይ የሰው ውሻ ምኑን ኖርከውና
ያልጠቀምካቸው ለት መች ይጨነቁና
እህል ውሀ ነስተው ጤና ያሳጡና
ያችኑ ጎጆህን ጥለህ ትሄድና
ቤት አልባ አድርገው ያንከራትቱና

መድረሻ አሳጥተው ያሳድዱህና
ገድለው ይቀብሩሃል አበደ ይሉና።
ለዕለት ፍርፋሪ ስትንሰፈሰፍ
የሰጡህን ሁሉ ጓግተህ ስትልፍ
ባንተም ይዞርና የሠራኸው ግፍ
በሆድህ እኮ ነው ነፍስህ የምታልፍ።
ቡችሊት በተራሽ
ምናምን ሰጥተውሽ
አንዴ ቹ!! ካሉሽ
አንችም እንዳቅምሽ
ገደል ካልሆነብሽ
መቼም አትመለሽ፤
ቦጫጭቀሽ በጥርስሽ
በድምፅ አደናግረሽ
መብልሽን እያሰብሽ
ወንድም አይታይሽ
እህት አይታይሽ
ለአባት አትመለሽ
አርደው ሲጥሉልሽ
ቆራርጠው ሲሰጡሽ
ለራስሽ ከበላሽ
አንጀትም አይቀርሽ
ለናት የሚያሳሳሽ።
ያልህንሽው ለጌታሽ
ምን አለ በሕይወትሽ
ሁሉንም አውከሽ
ለራስሽም አልሆንሽ
ላንቺም አይሳሱልሽ ጨካኝ ነው ልባቸው
ለነሱ አገልግሎት ካላስፈለግሻቸው
ሴት ውሻ ነች ብለው አይቀር መጣላቸው።
አረ እናንተ ውሾች አስቡ እባካችሁ
ግለኛ መሆኑ ምን ሊያዛልቃችሁ
ጉድጓድ ብትምሱ ለየብቻችሁ
ለጊዜው ቢመስልም የተመቻችሁ
ሁሉ ሲደረመስ የት ትደርሳላችሁ ?
ይልቅ መቀበሪያ እንዳይሆንባችሁ።
አሁን በድንግዙ ያልተያያችሁ
ይባስ ቀን ሲጨልም አውሬ እንዳይበላችሁ።
እናንት የሰው ውሾቻ
ታማኝ አገልጋዮች
የሆድ ተገዥዎች
አትሁኑ ተላሎች
ተማሩ ከሌሎች።
ለየ ዕለት ጉርሳችሁ
በመንሰፍሰፋችሁ
እንኩዋን ልጆቻችሁ
እናንተ ራሳችሁ
ምን ተስፋ አላችሁ?
እስከመኖራችሁ
ዋስትናም የላችሁ።
የናንተ ብጤዎች
በርካታ እንስሶች
ያለማችን ውሾች
የሆድ ግዞተኞች
ኖረው ለሆዳቸው
ለፍተው ለጌታቸው
ውርደቱ ከፍቷቸው
ባንድነት ተባብረው
ሰንሰለት በጥሰው
መብት ተጎናጽፈው
ይብቃን ማለታቸው
እንደተፈጥሮዋቸው
መኖር ዋስትናቸው
ተከበረላቸው።
ተርቦ ተጠምቶ ዱር አድሮ ወገንህ
ወይ እንሰሳ መሆን ምንም አይሰማህ
ዛሬ አንጀትህ ርሶ ባይታወቅህ
ጭራህን ስትቆላ ቢያቆላምጡህ
በወንበራቸው ላይ ለታይታ ቢያኖሩህ
ያማሩ አልባሳት ጃኖ ቢያለብሱህ
በወርቅም ሰንሰለት ቢታሠር አንገትህ
ከቶ አልተቀየረም ተገዥነትህ።
ቡቻላንትህን ሁሉ እያወቅብህ
ዝንታለም በከንቱ ታሥሮ መበላትህ
የሰው ማስፈራሪያ ሆኖ መቅረትህ
ታፈረ ተብሎ መጠራት ቀርቶልህ
ከነቡችሊት ጋር ቆርጠህ ተነሥተህ
ለመጭው ትውልድህ ተስፋም አሳይተህ
አንተስ ብትከበር ምንድነው ሚያንስህ ?
እስቲ ነፃ ውጣ በውነት ታፍረህ
ዝንታለም ከማፈር በውሻነትህ።

--------///--------

ተፈራ ድንበሩ